የኢትዮጵያ

ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)

ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL (EHRCO)

አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ

# ከመንግስት ተገቢውን ትኩረት የሚፈልጉ የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮች

የካቲት 20/2015 ዓ.ም

## በወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን ውስጥ የተፈጸሙ የመብት ጥሰቶች

በሰሜን ኢትዮጵያ በነበረው የሰላምና ፀጥታ ችግር ምክንያት የወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን አስተዳደር የፈረሰ ሲሆን ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ እንደ አዲስ የዞን አስተዳደር የተቋቋመ ቢሆንም ነገር ግን በአካባቢው የፍ/ቤትና አቃቢ ህግ ቢሮዎች ተቋቁመው ስራ ያልጀመሩ በመሆናቸው ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ የሰዎች ያለአግባብ እስር እየተፈፀመ መሆኑን እና በአካባቢው የሚገኙ እስረኞች ክስ ሳይመሰረትባቸውና ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ለረጅም ጊዜ ማለትም ከሁለት ወር እና ከዚያ በላይ ታስረው እንደሚገኙ ፤የገንዘብ አቅም እና ቤተሰብ ያላቸዉ የተወሰኑ እስረኞች ወደ ጎንደር ከተማ ጠቅላይ ፍ/ቤት ምድብ ችሎት በመቅረብና የአካል ነፃነት አቤቱታ በማቅረብ መለቀቅ የቻሉ ቢሆንም ነገር ግን በአካባቢው ያለው የአስተዳደር አካል በተደጋጋሚ የዋስትና መብታቸው እንዲጠበቅ ትዕዛዝ የተሰጠላቸውን እስረኞች ለመልቀቅ ወይም የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለማክበር ፈቃደኛ ባለመሆኑ በቀን 24/02/2015ዓ.ም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ጎንደር ምድብ ችሎት ጉዳዩ ከአቅሙ በላይ መሆኑን ገልፆ የሚመለከተው አካል መፍትሄ እስኪሰጥ ድረስ ይህንን ጉዳይ የማያስተናግድ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ በማውጣት ያሳወቀ መሆኑን እንዲሁም ይህ ጉዳይ የሰዎችን ፍትህ የማግኘት መብት ለማስጠበቅ የፍትህ ተቋማት ስራቸውን በአግባቡ መስራት ባለመቻላቸው መሆኑንና ለእስር የተዳረጉ ሰዎችም ያለምንም ከሳሽ በፖሊስ ጣቢያ ታስረው እንግልትና ድብደባ እየደረሰባቸው ለረጅም ጊዜ ማለትም ከሁለት እስከ ዘጠኝ ወራት ታስረው እንደሚገኙ ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለማወቅ ችሏል፡፡

## በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን እና አዋሳኝ አካባቢዎች የተከሰተ ረሀብን ተከትሎ የተስተዋሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

በኦሮምያ ክልል በቦረና ዞን እና አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ ለረጅም ጊዜ በቆየው ድርቅ ምክንያት በርካታ የጋማና የቀንድ ከብቶች መሞታቸውንና አሁንም ችግሩ እየቀጠለ እንደሚገኝ፣ በዚሁ ችግር ምክንያት ማህበረሰቡ በምግብ እጦት በከፋ ችግር ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የምግብ አቅርቦቱም በቂ ባለመሆኑ ዜጎች ስጋት ውስጥ መሆናቸውንና ለእንስሳትም እየቀረበ ያለው መኖ በቂ ባለመሆኑ ምክንያት በየቀኑ የሚሞቱ እንስሳት ቁጥር እየጨመረ እንደሚገኝ፣ ለእዚህም ከባድ ችግር ከመንግስት እየተደረገ ያለው ድጋፍ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ በምግብ እጥረት ምክንያት በችግር ውስጥ የሚገኙትን የአካባቢውን ነዋሪዎችና ከብቶቻቸውን ለመርዳት ከባድ እንደሚያደርገውና ከምግብ አቅርቦቱ በተጨማሪ የመድሀኒት፣ የእናቶችና የህጻናት አልሚ ምግቦች በከፍተኛ ሁኔታ በአስቸኳይ የሚያስፈልግ መሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

## ተያያዥ የህግ ግዴታዎች፡

የሰብዓዊ መብቶች ዓለም አቀፍ መግለጫ(UDHR) እና የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን(ICCPR) ሁለቱም ስምምነቶች በአንቀጽ 9 ላይ ማንም ሰው በዘፈቀደ ሊያዝ እንደማይችል፣ ማንም ሰው ከህግ ውጪ እንደማይያዝ፣ እንደ ማይታሰር እና የግል ነጻነቱን እንደማያጣ ይደነግጋሉ፡፡ በተመሳሳይ የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች ስምምነት አንቀጽ 6 ላይ በተመሳሳይ ማንም ሰው የነጻነትና የአካል ደህንነት መብት እንዳለው ይህንንም መብት ከህግ አግባብ ውጪ እንደማያጣ እና ማንም ሰው በዘፈቀደ ሊታሰር እንደማይገባ ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል ዓለም

አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን(ICCPR) አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ3 በወንጀል ክስ የተያዘ ወይም የታሰረ ሰው ከዳኛ ወይም በህግ ስልጣን ከተሰጠው አካል ዘንድ በአፋጣኝ ሊቀርብ እንደሚገባ ይደነግጋል።

የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 19(3) የተያዙ ሰዎች በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አላቸው። ይህምጊዜ ሰዎቹ ከተያዙበት ቦታ ወደፍርድ ቤት ለመምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም። ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረቡ በተጠረጠሩበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽላቸው መብት እንዳላቸው ይደነግጋል:: በተጨማሪም አንቀጽ 37 ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋል። ስለሆነም በእዚህ አንቀጽ መሰረት ሰዎች ፍትህ የማግኘት መብታቸውን መለማመድ ይችሉ ዘንድ መንግስት አስፈላጊ የሆኑ የፍትህ አካላትን እንደ ፍርድ ቤትና የአቃቤ ህግ ቢሮዎችን ለሰዎች ተደራሽ በማድረግ የሚሟላት ኃላፊነት እንዳለበት መረዳት ይቻላል።

የሰብዓዊ መብቶች ዓለም አቀፍ መግለጫ(UDHR) አንቀጽ 25 ማንም ሰው ለእራሱና ለቤተሰቡ ጤንነትና ደኅንነት በቂ በሚሆን የኑሮ ደረጃ የመኖር መብት እንዳለውና ይህም ምግብ ማግኘትን እንደሚጨምር ይደነግጋል። የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባሕላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን (ICESCR) አንቀጽ 11 ማንኛውም ሰው በቂ ምግብ የማኖኘት መብት እንዳለውና ሳይራብ የመኖር መሰረታዊ መብት እንዳለው ይደነግጋል። ሰዎች ከራሳቸው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ነገር ምክንያት ምግብ የማግኘት መብታቸውን መለማመድ በማይችሉበት ወቅት መንግስት ምግብን በማቅረብ የማሟላት ሀላፊነት እንዳለበት መረዳት ይቻላል። በተጨማሪም የአፍሪካ ኮሚሽን በግለሰቦች እና ሕዝቦች መብቶች በሰጠው ትርጉም ምግብ የማግኘት መብት በተዘዋዋሪ በህይወት በመኖር መብት፣ በጤና መብትና በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ የመልማት መብቶች አማካኝነት ጥበቃ እንደሚያገኝ ይገልጻል።

### የኢሰመጉ ጥሪ፡

- መንግስት በወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን በፍርድ ቤትና አቃቤ ህግ እጦት ምክንያት እየተጣሰ ያለውን ፍትህ የማግኘት መብትና እየደረሰ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲያስቆም፣
- በወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን የሚመለከተው የፍትህ አካል በፍርድ ቤት የዋስትና መብታቸው እንዲጠበቅ ትዕዛዝ የተሰጠላቸውን እስረኞች በአስቸኳይ እንዲፈታ፣
- የወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን አስተዳደር ለረጅም ወራት ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ታስረው የሚገኙትን ሰዎች ፍርድ ቤት በማቅረብ ፍትህ የማግኘት መብታቸውን እንዲያስጠብቅ፣
- በኦሮምያ ክልል በቦረና ዞን እና አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ በተከሰተው ድርቅ ምክንያት በርካታ የቀንድና የጋማ ከብቶች የሞቱ ሲሆን እስካሁን የሰው ህይወት አለመጥፋቱን የሚመለከተው የኦሮሚያ ክልል መንግስት አካል የገለጸ ቢሆንም ችግሩ ግን በዚህ የሚቀጥል ከሆነ በማህበረሰቡ ላይ የሚፈጠረውን ችግር የከፋ ስለሚያደርገው መንግስት ለጉዳዩ በቂ ትኩረት እንዲሰጥ፤
- በኦሮምያ ክልል በቦረና ዞን እና አዋሳኝ አካባቢዎች የሚከሰተው ድርቅ እና ረሀብ በተደጋጋሚ ጊዜ መከሰቱ የክልሉም ሆነ የፌደራል መንግስት ለጉዳዩ በቂ ትኩረት አለመስጠቱን የሚያሳይ በመሆኑ አሁን ለተፈጠረው ችግር በቂ ትኩረት በመስጠት ዜጎች ካሉበት ርሀብና ችግር የሚወጡበትን አስቸኳይ መፍትሔ እንዲያበጅ፣
- የኦሮሚያ ክልል መንግስት በድርቁ ምክንያት ለተፈናቀሉና ከፍተኛ ችግር ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች አስቸኳይ ድጋፍ እንዲያደርግ
- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዋግህምራ ዞን በሰቆጣ እና አካባቢው እንዲሁም በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ብርሀን ከተማ እና አካባቢው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተፈናቃዮች ከተለያዩ አካባቢዎች በግጭት ምክንያት ተፈናቅለው በከፍተኛ ርሀብ እና ችግር ውስጥ በመሆናቸው እና ከመንግስት በኩል እየተደረገ ያለው ድጋፍ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ መንግስት ተገቢውን በቂ ትኩረት በመስጠት አስፈላጊውን ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲያደርግ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል።

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ